# ይድረስ ........ ለ አቶ ግርማ ሰይፉ

ድንገት ወለድ በሆነ አጋጣሚ በ2002 ዓ.ም በተካሄደው የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ምርጫ ላይ በመወዳደር ለተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች መጽናኛ ለመሆን የበቃውን አንድ የውክልና መንበር ለማግኘት የቻሉት ብቸኛው የተቃዋሚ እንደራሴ ክቡር አቶ ግርማ ሰይፉ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እያሳዩ ያለው ፈንገጥ ያለ ባህሪይ ብዙዎቹን እያነጋገረ ነው፡፡

አገሪቱ አሁን ያለውን ሁለንተናዊ ለውጥ እንድታገኝ ለማስቻል በተካሄደው መራር የትጥቅ ትግል የተሰውትንና በዚህ ትግል አልፈው እዚህ የደረሱትን ኢትዮጵያዊያን ታጋዮችን ከፍተኛ የመንግስት ተቋማትንና ባለስልጣናትም የሽብር ጥቃት ሰለባ የሆኑ ወገኖችንና እነሱን ተከትሎ በአላማቸው የተሰባሰበውን ህዝብ ‹‹እስከመጨረሻው ድረስ አብረን እንታገላለን!›› ብለው ቃል በመግባት አብረዋቸው የተሰለፉ ታላላቅ የፖለቲካ መሪዎችን በተለያዩ ወቅቶች በሚጽፏቸው ጽሁፎች አልያም በሚሰጧቸው ቃለ ምልልሶች ክብረ-ነክ እና አጉራ ዘለልመልዕክቶችን በማስተላለፍ ቅርፀ ስብዕናቸውን ለመገንባት ቆርጠው የተነሱት አቶ ግርማ እየሄዱበት ያለው መንገድ የሌሎችን ክብር የሚሰብር ሆኖ ቢታይም እንኳን የአንዲት ሀገር ታላቁ አካል የሆነው የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባል በመሆናው ሊከበሩ የሚገባ ግለሰብ ናቸውና የተሰጣቸውን ክቡርነት ልነፍጋቸው አልሞክርም፡፡

በአልባሌ ባህሪ ተይዞ የሰዎችን፣ የባለ ስልጣናትንና የታላላቅ ተቋማትን ክብር መናድ አንቱታን የሚያነጥቅ ቢሆንም እንኳን የምርጫ ድምጽ የሰጣቸውን ህዝብ የምርጫ ውጤቱን ያፀደቀውን አካል፤ የምርጫ ውጤቱን ተቀብሎ ተገቢውን ቦታ የሰጣቸውን መንግስት፣ ይህንን ይሁንታ የሰጣቸውን መንግስት የሚመራውን አሸናፊ ፓርቲ፤ የሀገሪቱ የመጨረሻ አካል የሆነውን ምክርቤቱን እና ከሁሉም በላይ ደግሞ በምርጫ ስርዓት መወዳደርና አሸንፎ የዚህ ታላቅ አካል አባል መሆን የሚቻልበትንና ተቃውሞአቸውን በዴሞክራሲያዊ መንገድ መግለጽ የሚችሉበትን የመደራጀትና የመሰባሰብ መብት የተጎናፀፉበትን መልካም እድል ለመፍጠር የታገሉና በትግሉም ወቅት የወደቁ ጀግኖች ሰማዕታት ዝቅ ማድረግ በመሆኑ አንቱታቸውን አክብሬ መክነው የታዩበትን የሃሳብ ዝቅጠቶች ለመጎንተል እሻለሁ፡፡

የአቶ ግርማ ሰይፉን የተሳሳተ ስብዕና ከግል ባህሪያቸው ተነስቶ ማሳየት ቢቻልም ግላዊ ማንነታቸው በማጀታቸው የሚወሰን በመሆኑ እሱን በማለፍ ከተለያዩ አካላት ጋር በሚያነካካቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ ባተኩር ይበቃል፡፡ ከፓቲያቸው እንቅስቃሴ አኳያ ብንነሳ ምንም እንኳን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ከኪሳራ ውጪ ትርፋማነትን አግኝተው ባያውቁም ባደረጉት ተሳትፎ አንቱታን ያገኙ  የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን በመጎንተል በማዋረድ የሚታወቁ እኚህ ግለሰብ የፓርቲያቸውን ውስጣዊ አሰራር በተደጋጋሚ ጊዜ ለመናድ የበቁ ናቸው፡፡

ምንም እንኳን የሚሰነዝሩባቸው ትችቶች ትክክል ይሁኑም አይሁኑም በበሰለ ህሊና አገናዝበው እጅግ ትሁት በሆነ አንደበትና በሰለጠነ መንገድ መፍታት የሚጠበቅባቸው እኚህ ግለሰብ ‹‹የአዲሱ ትውልድ ፖለቲከኛ›› ነኝ ተብዬ ከራሳቸው ፓርቲ አመራሮች ጋር የሚደርስባቸውን ተቃውሞ በትችትና ሞራል ነክ በሆነ ስድብ ለመግታት መሞከራቸው ያሳፍራል፡፡

‹‹የተመረጡበት አካሄድ ግልጽ አይደለም›› የሚል ተቃውሞ በማቅረብ የፖለቲካ ጭፍራቸው መስመር የሳተ መሆኑን ለመግለጽ የሞከሩ አንድ ከፍተኛ የፖለቲካ ሰው የሰጡትን አስተያየት መነሻ በማድረግ ጉዳዩን እንደ ድርጅት ወስኖ በውስጥ ማየት ሲገባ አደባባይ ላይ በማውጣት እሳቸው በተደጋጋሚ ጊዜ ‹‹ወሮበላ›› እያሉ ከሚገልፁት ግብር በዘቀጠ ምግባር ስድባቸውን

ሲያኾርጎደጉዱት ማየት በእውነትም የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሰጣቸው ‹‹ክቡር›› የሚለው ማዕረግ ይመጥናቸዋል ወይ? ብሎ ለመከራከር የሚያበቃ ነው፡፡

በአጭር ጊዜ ጉዞ ከታላለቆቹ የተቃዋሚ ፖለቲካ መሪዎች የላቀ ሆኖ ለመቅረብ የሚደረገው ጥረት ጎልቶ የሚታይባቸው አቶ ግርማ ከሁሉ በባሰ መልኩ ዕድሜያቸውን በፖለቲካው ትግል እንዲሁም ከፍተኛ የትግል ጉዞ የፈጁ ታላላቅ መሪዎች ባሉበት አገር የአጭር ጊዜ የህይወት ተሞክሮዋቸውን ዳጎስ ባለ መጽሀፍ አሳትመው ለማቅረብ መቻላቸው ‹‹ልጅ ለናቷ ምጥ አስተማረች!›› አይነት ተረት ለማስተረት ከመብቃቱ በላይ የሰውየውን ነጋዴያዊ ስብዕና በተጨበጠ መልኩ ለማሳየት በቅቷል፡፡

በተሳሳተ የፖለቲካ አቋም ለመደንከር የሚሹት አቶ ግርማ የአጭር ጊዜ የፖለቲካ ጉዞአቸው ያፈጀና ያበቃለት ዘዴ መሆኑን በተደጋጋሚ ወቅት በሚሰነዝሯቸው ሃሳቦቻቸው የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ በቅርቡ ፓርቲያቸው ያደረገውን ሰላማዊ ሰልፍ ተከትሎ በአይጋፎረም ላይ የሰነዘሩት አስተያየት ምን ያህል በአጭር ጊዜ ውስጥ ዘቅጠውና ወርደው ማብቃታቸውን በተጨበጠ መልኩ አረጋግጧል፡፡

ሰውዬው ‹‹ክቡር ጠቅላይ ሚኒስተር ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ይህንን የማፍያ ቡድን በማፍረስ ታሪክ ይስሩ›› በሚል ርዕስ በጻፉት ጽሁፋቸው ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት፣ የስብሰባ እና የመደራጀት ነጻነት፤ የሰጣቸውን አካል ብሎም ባለፈው እሁድ መስከረም 19/2005 ዓ.ም ፓርቲያቸው ያደረገውን ሰላማዊ ሰልፍ የፈቀደውን መዋቅር መልካም ተግባር በማሳነስ ‹ማፊያ›› እያሉ በመግለጽ መሳደባቸውን አስነዋሪነታቸውን ያረጋገጠ ከዚያም አልፎ በአለማችን ላይ ተስፋፍቶ የሚታየውን የማፍያ ቡድኖች ምንነት በተመለከተ ከአራተኛ ክፍል ተማሪ ያነሰ እውቀት እንዳላቸው ያመላከተ ሆኗል፡፡

‹‹ጠቅላይ ሚኒስተር ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ከበረሃ ይዘውት የመጡት ልዩ ልዩ የአፋኝ ቡድን ስለማይኖራቸው እንዲሁም ቀደም ሲል የነበሩትን አፋኝ ቡድኖች ወደ አንድ መቀየርና ማጠቃለል ተጠሪነቱ ከተለያዩ መዋቅሮች ወደ ጠቅላይ ሚኒስተርነት ቁጥጥር በማስገባት.... ›› የሚለው የፀሃፊ ተብዮው የአቶ ግርማ ሃሳብ የባከኑ ሆነው መታየታቸው ብቻ ሳይሆን ድፍረት የተሞላቸው ክህደቶች መሆናቸውን መጥቀስ ተገቢ ነው፡፡

በመራር የትግል ሂደት በተከፈለው ከፍተኛ መስዋዕትነት በተገኘው የመምረጥና የመመረጥ መብት ተጠቅመው የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባል ለመሆን የበቁት አቶ ግርማ ለዚህ መብት ያበቃቸውን የመስዋዕትነት ውጣ ውረድ እንዲሁ ሳምሶናይት ይዞ መንገድ በማካለል ለተፈጠረ አለሌ ስነ ምግባራቸው ‹‹ አፋኝ›› ሲሉት መጥራታቸው አሁንም ቢሆን ደጋግሜ ከህግ ጋር ላለመጋፋት ም/ቤቱ የሰጣቸውን ስልጣን ወይም ክብር ላለመጋፋት ስል ብቻ እንዳከብራቸው ብገደድም የዘቀጡና የረመጡ መሆናቸውን ያሳየኝ መሆኑን አልክድም፡፡

የስልጣን ተጠቃሚ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባልነትና ልዩ ልዩ መብቶችን የሰጣቸውን የትግል ጉዞ ‹‹አፋኝ›› ብለው መጥራታው ያላነሳቸው አቶ ግርማ እነዚህን ‹‹አፋኝ ቡድኖች ወደ አንድ መዋቅር በማጠቃለል ተጠሪነቱን ከተለያዩ መዋቅሮችና ግለሰቦች ወደ ጠቅላይ ሚኒስተሩ...››› የማድረግ እቅድን ማመላከታቸው ‹‹ለምን ብዙ አፋኞች ይኖሩናል? በአንድ መዋቅር ሚመራ አፋኝ ብቻ ይበቃናል›› ማለታቸው ይሆን? ብዬ እስክጠራጠር ድረስ ደግሜ... ደግሜ.... ደግሜ ባነበው አልገባህ አለኝና የሰውየው የሀሳብ መሀንነት ወለል ብሎ ታየኝ፡፡

ፖለቲከኛም ጸኃፊም ነኝ ተብዬው በተጠቀሰው ጽሁፋቸው በተደጋጋሚ ጊዜ ‹‹መንግስታችን›› እያሉ መጥቀሳቸው ስለ ፖለቲካ እውቀት እንደሌላቸው በተጨባጭ ያሳያል፡፡ ‹‹አቶ ግርማ እርስዎ መንግስታችን እያሉ የሚጠሩት አሁን ኢትዮጵያን እያስተዳደረ ያለው መንግስት የተመሰረተው እንዴት ነው?›› ይህንን አካል ‹‹መንግስታችን›› ካሉ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አብላጫ ወንበር ይዞ መንግስት የመሰረተውን ኢህአዴግን እየጠሩ መሆኑን ካሰቡት ይህ ማለት ደግሞ ኢህአዴግ በመሰረተው መንግስት ይተማመናሉ ማለት ነው፡፡

ኢህአዴግ የመሰረተውን መንግስት የእኛ ብለውእየጠሩ ይህንን ድርጅት ከበረሃ አንስቶ በከፍተኛ መስዋዕትነት ለዚህ ያበቁትን ውድ ታጋዮች ‹‹አፋኝ ሀይሎች›› ብሎ መጥራት እንዴት ይቻለዎታል? ከዚህ አጠቃላይ ነጥብ ስንነሳ በዚህ መስዋዕትነት የተገኘውን ውጤት እየቀመሱ መስዋዕትነቱን ማጣጣል የሚዋጥ አይደለም፡፡ በዚህ መስዋዕትነት የተገኘውን መንግስት ‹‹መንግስታችን›› እያሉ መንግስት የዘረጋውን መዋቅርና ሌሎች አካላትን ነጣጥሎ መኰንተል የፖለቲካ አባዜም መሰልጠን ሳይሆን መሰይጠን ነው፡፡

አቶ ግርማ በሰልፉ ዕለት ፖሊሶች ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን እንደጠየቁዋቸውና እሳቸውን በማጥላላት ሰልፉን ለማስቀረት ሞክረው እንደነበረ በዚሁ ጽሁፉው መጥቀሳቀቸው ያሳፍራል፡፡ በእሳቸው መንገላታት የአንድነት ሰልፍ የሚስተጓጎል ከሆነ ፓርቲው ዕውን አለ ወይ? እስከማለት ያደርሰናል ለረጂም አመታት በፖለቲካ ውስጥ ልምድ አለን የሚሉ ሰዎች በሰልፉ ላይ ከፊት ቆመው በእሳቸው መንገላታት ሰልፉ ሊከሽፍ እንደነበረ ማስረዳታቸው ‹‹ከኋላ የመጣ አይን ያወጣ›› የሚለውን አባባል አስታውሶኛል፡፡

በሰልፉ ዕለት አቶ ግርማ ‹‹ማፊያ›› ብለው የጠሩዋቸው የፀጥታ ኃይሎች የወጣቶችን ፎቶ ይዘው ወጣቶችን ሲያድኑ እንደነበሩ በመጥቅስ ‹‹በዕለለቱ ለወጣቶቹ ደህንነት ሲባል በአጀብ ወደ ቤታው ለማድረስ ቻልን ቢሆንም›› ማለታቸውን ላስምርበት ወደድኩ፡፡ አቶ ግርማ ለመሆኑ ወጣቶቹን ወደ ቤታው ያደረሱዋቸው በምን አይነት አጀብ ነው? አንድነት እርስዎ ከገለጹልን ከበርሃ ጀምሮ ትጥቅ ይዞ ተዋግቶ ቤተ መንግስቱን ተቆጣጥሮ እስከ አሁን ድረስ ኢትዮጵያን እያስተዳደረ ካለው የ‹ማፍያ› ቡድን ክትትል ውጪ የሚያደርግ የታጠቀ አጃቢ ሀይል አለው ማለትዎ ነው?

ከሁሉም በላይ የእኚህ ግለሰብ አሳፋሪነት በሀይማኖት ጉዳይ ላይ ያላቸውን የመሀይምነት መጋረጃ አለመቀደዱን ያሳዩበት ነው፡፡ ጊዜያቸውን በጠለቀ ጥናትና ምርምር እንዲሁም በተካነ የፖለቲካ ስብዕና በማጥፋት እዚህ ለደረሱት ጠቅላይ ሚኒስተር ሀ/ማሪያም ደሳለኝ ከመንደርተኛ ስብዕና በተቀዳ መረን ለቀቅ አመለካከት ምክር ቢጤ ለመስጠት የወደዱት አቶ ግርማ ይህንን መረን ለቀቅ አቋማቸውን ‹‹ይህን ማድረግ የሚያስችል (የማፍያ ቡድን የማፍረስ) ስልጣን ከሌለዎት ስለ ሀገር ክብር የሚሰጠውን የክርስትና እምነት እየተከተሉ ይህን ስልጣን መያዝ ትርጉም ስለሌለው .....›› በማለት ይገልጹታል፡፡ የተከበሩ አቶ ግርማ ሌሎች ሀይማኖቶች ለሰብአዊ ፍጡር ክብር የላቸውም ወይ? ይህ አቋም ብቻ መንደርተኛነታዊ አቋሙዎን ከማሳየቱም በላይ ሊቀ መንደር መሆንዎን በተጨባጭ ያረጋገጠ ነው፡፡

በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ውስጥ የጥፋት እሳት ለማንደድ እየተረባረቡ ያሉ ወገኖች አሉ ከእነዚህ ወገኖች መካከል ደግሞ የህይወት ሁሉ መሰረታዊ ፍላጎት በሆነው ሰላማዊ ውሃ ውስጥ ተቀምጠው የተፈጠረላቸውን መልካም ዕድል እያመሰገኑ የትግል አቅጣጫቸውን ስለ ማስፋት የሚያልሙ ጥቂቶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡

እነዚህ ሀይሎች የውሃው ምህዳር የፈጠረላቸውን አለም ተረጋግተው እራሳቸውን ከማስፋ ይልቅ ‹‹ብርዱ … ብርዱ!›› እያሉ በማማረር መልካም ዕድሉን ያመቻቸላቸውን አካል ምስጋና መንሳታቸው የእንቁራሪቷን ታሪክ ማስከተሉ አይቀርም፡፡

ዕንቁራሪቷ ተረጋግታ በተቀመጠችበት ውሀ ውስጥ ‹‹ብርዱ… ብርዱ… ብርዱ!›› እያለች ታማርር በነበረበት ሰዓት ከሷ ጥቂት ራቅ ብሎ በሚገኘው መንደር የተነሳውን እሳት ለማጥፋት ባልዲ ይዘው የሚመጡ ሰዎች ያለችበት ቦታ ይደርሳሉ፡፡ እናም ከተሞላው ውሀ ጋር በአንድ ባልዲ የገባችው እንቁራሪት  ባልዲ ውስጥ እያለች ‹‹ብርዱ…. ብርዱ… ብርዱ!›› እያለች ወደ ሚነደው እሳት ከውሀው ጋር አብራ ተደፍታ አረፈችው!!

አዎን! ኢትዮጵያ ውስጥ የአክራሪነትን እሳት ሊያቀጣጥሉ የሚፈልጉ የጥፋት አሳቶች አሉ፡፡ እነዚህ እሳቶች ግን እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ በታጋዮች መስዋዕትነት እና በንፁኃን ዜጎች ደም የሚጠፉ አይደሉም የሚጠፉት እሳቱን ያቀጣጣጠሉት አካላት በራሳቸው እሳት ነደው እንዲያልቁ በማድረግ ነው!